ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ሰላምነ

ዘረሰዮሙ አሐደ ለክልኤሆሙ ፤ ኤፌ ም ፪ ቍ ፲፬

፲፰ኛ ዓመት ቍጥር ፯

አ ፤ አ ፤ ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ. ም.

# ተክለ፡ሃይማኖት።

ይህ ድርሰት ለሃይማኖትና ለምግባር ለጊዜውም ዜና መዋዕል መግለጫ የንባቡን ቀጥተኛ ትርጓሜ ከመከተል ጋር ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ መታሰቢያ
ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ተሰየመ ።

| የድርሰቱ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 1.20<br>» » አንዱ 0.5<br>ለውጭ አገር እጥፍ ይሆናል ። | በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክና ዜና ማደራጃ<br>ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት ታተመ ። | በወር ሁለት ጊዜ ይወጣል ።<br>የስልክ ቍጥር 13090|4<br>የፖስታ ሣጥን ቍጥር 12.83 |
|---|---|---|

## ታ ቦ ተ ጽ ዮ ን ።

ታቦትን የምናከብርበት ምክንያት ከዚህ እንደሚከተለው ነው ። በዚህ ዓለም የምንኖር የአዳም ልጆች አንዳንድ የማይናወጽና የጠበቀ ፤ ለመለወጥም የማይቻል ሕግ እንዳለን የሚታመን ነው ። ይህም ሕግንና ባህልን የመሰለ ሲሆን ፤ ከዚህ ላይ አንዱን ልጠቅሰው እወዳለሁ ። እንደሚታወቀው በልዩ ልዩ ውለታዎች የምንሠራበትና የምናጸናበት ቃል ዕውነተኛነቱ ተጣርቶ ከተረጋገጠ በኋላ እንዳይፈርስና ለዘለዓለም ጸንቶ እንዲኖር ፤ እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ በማለት ውለታችንን እጠንክረን ፤ መሬትም እንደሆነ ክርታስንሥትን የውሉ ቃል ቦክብር ሙዝገብ ሰፍሮ እንደሚቀመጥና ለኋላ ምስክር እንደሚሆን ሁላችንም እናውቃለን ።

እኛም ክርስቲያን የሆን ሰዎች ይህ በየጊዜው የምናከብረው ታቦት የእግዚአብሔርን ዕውነተኛውን ቃል ኪዳኑን ይዞ ስለተገኘ ነው እንጂ ለከንቱ አይደለም ። እግዚአብሔር ለአዳም ልጆች በታቦቱ ላይ ፲ቱ ቃላትን ጽፎ በሙሴ እጅ ሰጣቸው ። ሰዎቹም እነዚህን ቃላት ሊጠብቁ ፤ እግዚአብሔርም ለጊዜው ምድረ ርስትን ፤ ኋላም መንግሥተ ሰማያትን ሊያወርሳቸው ቃል ኪዳኑ ከሕዝቡ ሁሉ ጋር ሆነ ፤ ሕዝቡም እንዲጠብቋቸውና እንዲያከብሯቸው ዓሠርቱ ቃላትን ጽፎ እንደ ሰጣቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ። ዘፀዐት ፳ ፣ ፲፯ ሌዋውያን ፲፬ ፣ ፲፰

አባቶቻችን በቈዩን መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ሳታቋርጥ ከምእመናን ጋር በመስማማት እነሆ ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣውን ታቦተ ጽዮንን በየዓመቱ፤ በየቦታው ታከብራለች ። የአከባበሩም ሁኔታ ካህናቱ በከበሮ ፤ በጸናጽል ፤ በሽብሻቦ ፤ ሕዝቡም በሰልፍና በሆታ ፤ በእልልታ የሚያከብር መሆኑን ሁላችንም እንዘነጋውም ። እኛስ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ የምናከብረው ከምን ያገኘነው ነው ? የሚል ጥያቄ ቢገጥመን መልሱ ይኸውና ፤ እስራኤል በእግዚአብሔር አዛዥነት ፤ በኢያሱ መሪነት ፤ በታቦተ ጽዮን አሸናፊነት ወደ ኢያሪኮ ሲገቡ እግዚአብሔር ለኢያሱ ታቦትን እንዴት እንደሚያከብር ዘርዝሮ እንዳመለከተው መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ ስድስትን ብናነብ በሰፊው እንረዳለን ኢያሱ ፮ ፣ ፪—፲)

ቀድሞ እንደ ፳ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጦርነቱ በጀት ፤ በሐይድሮጂን ፤ በኑክሌር ፤ እንዲሁም ልዩ ልዩ በሆኑ አሰቃቂ መግሪያዎች ሳይሆን እግዚአብሔርን በመለመንና እሱን በማምለክ ፤ ታቦተ ጽዮንን መሣሪያ በማድረግ ስለነበረ ፤ እስራኤል ከፍልስጥኤማውያን ጋር ጦርነት ባደረጉ ጊዜ የእግዚአብሔርን ታቦት ይዘው በመሰለፍ ጦርነት እንደአደረጉ ፩ኛ ሳሙኤል ፬ ፣ ፫ ይነግረናል ። ሆኖም እስራኤላውያን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳይጠይቁ በመነሣታቸው ግማሾቹም እሱን ትተው ጣዖት በማምለካቸው ምክንያት ምንም እንኳን የማቸነፍ ዕድል ባያጋጥማቸው የእግዚአብሔር ታቦት ኃያል ሥራ ከመሥራቷና ጠላቶቻቸውን ከማቸነፍ አላቋረጠችም ፤ ዛሬም አይቋረጥብንም ፤ የእስራኤል ጠላቶች የሆኑ ፍልስጥኤ

ተከታዩን በ፫ተኛው ገጽ ይመልከቱ ።

## « በ ቀ ለ ደ ሞ ሙ ለ እ ግ ብ ር ቲ ከ ዘ ተ ክ ዕ ወ የፈሰሰው የባሮችህ ደም በቀል » ።

ከዲበ ኵሉ ዘውዴ

ስለ ክቡር የዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ፕሬዚደንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ በዋሽንግተን የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት በሚፈጸምበት ዕለት ኅዳር ፲፮ ቀን ፶፮ ዓ. ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አዲስ አበባ በመንበረ ጸባኦት ቅ| ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐት አድርሳላቸዋለች ። በዋሽንግተን ዲ. ሲ. በሚፈጸመው የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ላይ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀ. ኃይለ ሥላሴ እንደ መገኘታቸው መጠን በዚህኛውም ሥነ ሥርዓት ላይ ልዑል አልጋ ወራሽ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ተገኝተዋል ።

በሥነ ሥርዓቱም ላይ ዲያቆኑ «ወይርዓዩ አሕዛብ በቅድመ አዕይንቲነ በቀለ ደሞሙ ለአግብርቲከ ዘተክዕወ ይበፅ ቅድሜከ ገዓሮሙ ለሙቁሓን ፤ የፈሰሰው የባሮችህ ደም በቀል በፊታችን በአሕዛብ ዘንድ ይታወቅ የታሠሩትም ልቅሶ (ጩኸት) ወደ አንተ ይግባ » የሚለውን ከዳዊት መዝሙር ሰበከ ። በውነቱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ክቡር ፕሬዚዴንት ኬኔዲ ምን ያህል ከፍ ያለ ግምትና አስተያየት እንደ ነበራት በግልጥ

ተከታዩን በ፫ኛው ገጽ ይመልከቱ ።

www.ethiopianorthodox.org

